የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF LABOUR AND SOCIAL AFFAIRS - ETHIOPIA

# የፌዴራል ቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ ለማቋቋም እና ተግባርና ኃላፊነቱን እንደገና ለመወሰን የወጣ መመሪያ ይዘትን አስመልክቶ የቀረበ አጭር ማብራሪያ

2013ዓ.ም

አዲስአበባ

## መመሪያው ማሻሻል አስፈላጊነት

የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድን ተግባርና ኃላፊነት ለመወሰን ከ1997 ዓ.ም. ጀምሮ ሲሠራበት የቆየው መመሪያ አዲስ ከወጣው አዋጅና ከወቅቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በተጣጣመና ለአሠራር ምቹ በሆነ አዲስ መመሪያ እንዲተካ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 171/2 በተሰጠው ሥልጣን ቀደም ሲል የመንግሥት የአሠሪዎች እና የሠራተኞች ማህበራት ተወካዮች በማካተተ ተቋቁሞ የነበረውን የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ተግባርና ሀላፊነት በዝርዝር እንደገና በመወሰን የአማካሪ ቦርድ ተሳትፎ ይበልጥ በማጠናከር የጎለበተ ምክረ-ሃሳብ ለማግኘት እንዲረዳ እና የተጠናከረ የሶስትዮሽ ማህበራዊ ምክክር ስርዓትን ለመዘርጋት ይህ መመሪያ ማሻሻያ ተዘጋጅቷል፡፡

## የመመሪያው ዝግጅት ሂደት

ከጠቅላይ አቃቤህግ፣ ከክልል እና ከተማ አስተዳደር ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ሀላፊዎች ፣ ከኢትዮጵያ አሠሪ ፌዴሬሽኖች ኮንፌዴሬሽን፣ ከኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበራት ኮንፌዴሬሽን፣ እና ከአማካሪ ቦርድ አባላት ጋር በተለያየ ጊዜያት በተካሄዱ የውይይት መድረኮች በተገኙ ግብዓቶች ረቂቅ መመሪያውን የማዳበር ስራ ተሰርቷል፡፡ በመጨረሻም የተዘጋጀው ረቂቅ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማኔጅመንት አባላት ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ በተሰጠ አስተያየቶች ዳብሮ እንዲፀድቅ ተደርጓል ፡፡

## የመመሪያው ዝርዝር ድንጋጌዎች

መመሪያው በአራት ክፍሎች እና 17 አንቀፀች አሉት፡፡ በክፍል አንድ ከአንቀፅ 1 እስከ አንቀፅ 4 ያሉት ድንጋጌዎች ጠቅላላ የሆኑ ጉዳዮችን የያዘ ሲሆን እነዚህም አዋጅ አንቀፅ 171/2 እና 3 መሠረት ቋሚ የሆነ የአማካሪ ቦርድ ከማቋቋም አንፃር በተዋረድ ለሚኒስትሩና በክልል አግባብ ላለው ባለሥልጣን በሕጉ ተለይቶ በተሰጠው ስልጣን መሠረት በፌዴራል በሚኒስትሩ የሚቋቋመው ቋሚ አማካሪ ቦርድ ተግባርና ሃላፊነቱን ለመወሰን የተዘጋጀ መመሪያ በመሆኑ በአንቀፅ1 የመመሪያው ስያሜ "የፌደራል ቋሚ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ ለማቋቋም እና ተግባርና ኃላፊነትን እንደገና ለመወሰን የወጣ መመሪያ በሚል ተቀምጧል፡፡ በተጨማሪም በትርጓሜ በያዘው አንቀፅ በመመሪያው ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉት ለተወሰኑ ቃላትና ሀረጎች ምን ለመግለፅ እንደታሰበ ትርጉም ተሰጥቷቸዋል፡፡ በዚሁ ክፍል አንቀፅ 3 የመመሪያው የተፈፃሚነት ወሰን የሚደነግግ ሲሆን በዚህም መመሪያው የአሠሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ማስፈፀሚያ ከመሆኑ አንፃር ከአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት በሚመነጩ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ እንደሚሆን ተገልፃል፡፡

የመመሪያው ክፍል ሁለት ከአንቀፅ 4 እስከ አንቀፅ 11 ያሉትን አንቀፆች የያዘ ሲሆን በዚህ ክፍል የተካተቱ ዋና ዋና ጉዳዬች መካከል በብዙ ሀገራት ህጎች እንደሚታየው እና ኢትዮጲያም ተቀብላ ካፀደቀችው የሶስትዮሽ ምክክር ስምምነት ቁጥር 144 ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር አሠሪና ሠራተኛ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ለሚኒስትር ሃሳብ (አስተያየት) የሚሰጥ የሠራተኛ ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ሰብሳቢ የሆኑበት ከመንግስት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ እና ሌሎች አግባብነት ካላቸው የመንግስት መ/ቤቶች ተወካዮች እና ከአሠሪና ሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን ተወካዮች በእኩል ቁጥር አባላት ያሉት አማካሪ ቦርድ እንደሚቋቋም እና አሠሪና ሠራተኞች ከመንግስት ጋር ተቀራርበውና ተመካክረው የሚሰሩበትን አሳታፊ የሶስትዮሽ የምክክር ስርዓት መዘርጋት የመመሪያው አላማ መሆኑን በአንቀፅ 4፣5 እና6 ተደንግጓል፡፡ በዚሁ ክፍል አንቀፅ 7 ከንዑስ አንቀፅ (1) እስከ ከንዑስ አንቀፅ (18) የአማካሪ ቦርዱ ምክረ-ሃሳቦችን የማመንጨት አቅም በማዳበር በምክክር የተገነባና የተጠናከረ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አስተዳደር ስርአት ለመፍጠር ቀደም ሲል አማካሪ ቦርዱ በማማከር ተግባሩ ከሚሳተፍባቸው ጉዳዮች በተጨማሪ በርካታ ከአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት የሚመነጩ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ተካተው የተዘረዘሩ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ በዋናነት የተቀናጀ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አስተዳደር ሥርዓት ለማጠናከር፣ የተሟላ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕጎችንና ፖሊሲዎችን ለማዘጋጀት፣ለማስተባበር፣ ለመከታተልና ለማስፈፀም ፣ የአገር ውስጥና የውጪ አገር የሥራ ሥምሪት አገልግሎት ስለሚስፋፋበትና ስለሚጠናከርበት ሂደት፣ የሥራ ሁኔታዎች መቆጣጠሪያ አገልግሎት ለማጠናከር በመንግሥት ፀድቀው በሥራ ላይ ያሉ የዓለም ሥራ ድርጅት ዓለም አቀፍ ስምምነቶችንና የሌሎች አቻ ሕጎችን አፈፃፀም ለመከታተልና፣ አሠሪና ሠራተኛን የተመለከቱ ደንቦችና መመሪያዎች በሥራ ላይ ከመዋላቸው በፊት ሀሳብና አስተያየት በመስጠት የማማከር ሀላፊነት ያለው መሆኑ ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም የውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፍቃድ አሰጣጥ፣ አፈፃፀምና የቁጥጥር ሂደት እና አጠቃላይ የኢንዱስትሪ ሰላም በማስጠበቅ በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት በዘላቂነት ለማራመድ የአሠሪና የሠራተኛ ተወካዮችም ከመንግሥት ጋር ተቀራርቦ በጋራ ለመሥራት የሚያስችሉ ጉዳዮች ተካተዋል፡፡

የመመሪያው ክፍል ሶስት ከአንቀፅ 11-14 ያለው ሲሆን በዚህም ክፍል የአማካሪ ቦርዱ ፅ/ቤት ተጠሪነት ለሚኒስትር ሆኖ አንድ ፅ/ቤት ሀላፊና ሌሎች አስፈላጊ ሰራተኞች እንዲኖሩት እና ቢሮው በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውስጥ እንደሚደራጅ ተገልፃል፡፡ በዚሁ ክፍል የአማካሪ ቦርዱን ተግባር የተሳለጠ ይሆን ዘንድ አንቀፅ 13 በጽሕፈት ቤቱ የሚከናወኑ ተግባርና ኃላፊነት የተዘረዘሩ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ስብሰባ ከመካሄዱ አስቀድሞ ለመነጋገሪያ የሚሆኑ አጀንዳ ጉዳዮችን ከዕቅድ በመለየት ለአማካሪ ቦርዱ ሰብሳቢ አቅርቦ ማፀደቅ፣ ስብሰባ የሚካሄድበትን ቀንና ሰዓት እንዲወሰን ማድረግ እና ሲወሰን አባላት እንዲገኙ ጥሪ እና የውይይት አጀንዳ ማስተላለፍ፣

የተደረጉ ምክክሮችና የተሰጡ ምክረሀሳቦችን የያዘ ቃለ-ጉባኤዎች ማዘጋጀት እና በአባላቱ ተፈርሞ በመረጃነት እንዲያዙ ማድረግ፣ቦርዱ መታየት ባለባቸው ጉዳዮች ላይ ለአማካሪ ቦርዱ ሰብሳቢ ሃሳብ ማቅረብ ሲፈቀድም በዕቅድ እንዲካተት ማድረግ፣ ዓመታዊ የአማካሪ ቦርድና የጽ/ቤቱን የሥራ ዕቅድ  እና ሪፖርት ማዘጋጀት እና ሌሎች በሚኒስትር ወይም በአማካሪ ቦርዱ ሰብሳቢ የሚሰጡትን ተጨማሪ ተግባራት በጽ/ቤቱ እንደሚከናወን ተዘርዝሯል፡፡ እንዲሁም በዚሁ ክፍል በአንቀፅ 14 የቦድር ፅ/ቤት ሀላፊ በቦርዱ በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት የጽ/ቤቱን ስራዎች ከመምራት፣ ከማስተባበር እና ከመቆጣጠር በተጨማሪም የአማካሪ ቦርዱን ሥራ ለማሳካት ያልተቋረጠ ጥረት የማድረግ ኃላፊነት  ያለበት መሆኑ ተደንግጓል፡፡

በመጨረሻም  ክፍል አራት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች በሚል ከአንቀፅ 15 እስከ አንቀፅ 14  የተደነገገ ሲሆን በዚህም ክፍል አባላትን የሚወክሉ ተቋማት (የአሠሪ እና የሠራተኛ ኮንፌዴሬሽን፣ አግባብነት ያላቸው የመንግሥት መ/ቤቶች) እና የአማካሪ ቦርድ አባላት ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ  እንዳለባቸው ፣ቀደም ሲል ቦርዱን ለማቋቋም በጥቅምት 17 ቀን 1997 ዓ.ም. የወጣው መመሪያ ስለመሻሩን እና መመሪያ ስለሚፀናበት ጊዜ በተከታታይ አንቀፆች ተደንግጓል፡፡